# አባ ዲያብሎስ

*ወንድሙ መኰንን*
*ለንደን*

አይ የስምንተኛው ሺህ ጣጣ፤
ባሕታዊ ከዋልድባ ታጣ?
መነኰሴ ከገዳም እንደጠፋ፤
ንግሡ አጋንንት ይስፋፋ?
ዘመን ያመጣብን ጣጣ፤
ዲያብሎስ ከኒው ዮርክ ይምጣ?
እንዳልኰነን ተጠንቅቄ፤
እንዳልረክሰበትም ርቄ፤
እርስዎ እያልኩኝ አውቄ፤
ዲያብሎስን ልጥራ ለጥያቄ።

በመለስ ጌታ አምላክዎ፤
በበረከት ስብሀት ረዳትዎ፤
በደፋት በነጩ በፍታዎ፤
በአጠለቁት ፀአዳ ጀለቢያዎ፤
ከወርቅ ባሠሩት መስቀልዎ፤
አባ ዲያብሎስ እባክዎ፤
ጥቂት ጥያቄ ላቅርብልዎ።

ዘዴ በልሀትም ባያጡ፤
እንዴት ከገሀነም አመለጡ?
በምን ታለለ መልዐኩ፤
እርስዎ ከሲያል ሲሾልኩ?

አሁንስ፤ ተመነጠቁ፤
በመሰሪይነትዎ ተራቀቁ፤
ከታሠሩበት ተለቀቁ፤
የዕርግማን ልብስዎን አወለቁ፤
ነጭ አክሴማም አጠለቁ።
ጆሮ ዘንድሮ ጉድ ሰማ፤
ጥቁር አልነበር አክሴማ?
ሳይገነዙ ሳይጉላሉ፤
በጎን አባ ተባሉ?

የሚገርመው፤

የእባብ ጸባይዎን አልደበቁ፤
መንታ ምላስዎን እይሰበቁ፤
የእግዚአብሔርን ሎጆች እያጠቁ፤
እንዴት ለእጬጌነት በቁ?
ንዋየ ቅድሳትን እያነደዱ፤
ፃድቃንን እያሳደዱ፤
የመነኰሳትን ደም እያፈሰሱ፤
ቅድስተ ቅዱሳትን እያረከሱ፤
ቤተ መቅደስ እያፈረሱ፤
እንዴት ለርዕስ ማዕረግ ደረሱ?
እንዴት በድፍረት ነገሡ?
በጎችን ነጥቆ የሚበላ፤
እረኛ ይሆናል ተኵላ?

ሹመት በማዕረግ እየገነኑ፤
በሥልጣን ድሎት እየፎነኑ፤
አባ ዲያብሎስ ሰይጣኑ፤
ምነው ሳይበቁ መነኑ?
ዓለምዎን እየቀጩ፤
እንዴት ለብፁዕነት ታጩ?

በጦር ሠራዊት ተከበቡ፤
በኮማንዶ ኃይል ታጀቡ፤
ከባድ መትረይስ ታጠቁ፤
ሽጉጥ በኪስዎ ድበቁ፤
አብረው በአንድ ኪስ አያኑሩት፤
ሽጉጡ፤ ያ የሰወሩት፤
እንዳይባርቅብዎት ሲመዙት፤
መስቀሉን በጅዎ ያዙት።
አባ ዲያብሎስ ተንኰሉ፤
እንዴት አሾፉ በመስቀሉ?

ገና ሳስበው ሰቀጠጠኝ፤!
ያ ቀን ሲመጣ እርስዎን አያርገኝ።
ሲላክብዎት ከላይ ታዞ፤
መልዐከ ሞት ሰይፉን መዞ።
የፍርድ ቀንዎ ሲደርስ፤
የለበሱት ገላ ሲፈርስ፤
ትጠብቅዎታለች ተዝናናታ፤
መቃብር አፏን ከፍታ።

PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com